# ሌሎች እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ መርዳት

# መግቢያ

ህይወት ጉዞ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይወድሀል፤በዚህ በህይወት ጉዞ ውስጥ ስኬታማ እንድትሆን ይፈልጋል፡፡ስኬት አንተን ጨምሮ በማንኛውም ሰው ህይወት ውስጥ አስደናቂውን የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትህ በመፈጸም ወይም ባለመፈጸም ይወሰናል፡፡በመረጥከው መንገድ ላይ በመሆን፤በዘለዓለማዊ መንግስቱ ውስጥ የተትረፈረፈውን በረከት እየተካፈልክ ልትፈጽም ትችላለህ ወይም በአንጻሩ ማለቂያ በሌለው ቅዠት ውስጥ ትኖራለህ፡፡ብሩህ የሆነውን መንገድ መርጠህ የእግዚአብሔርን ዓላማ ትፈጽም ዘንድ በየዕለት ህይወትህ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ይኖርብሀል፡፡ለዚህ ነው ይህ የመማሪያ መጽሐፍ አንተን ለመርዳት የተዘጋጀው፡፡

እያንዳንዱ ሦስት የትምህርት ክፍሎች አሉት: {1} የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤ {2} መሠረታዊ ጥያቄዎች፤እና {3} የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ ወይም ተግባራዊ ስራዎች ናቸው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በማወቅ እንድታድግ ይረዱሀል፡፡መሠረታዊ ጥያቄዎች ደግሞ በምታውቀው የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንድትኖር ይረዳሀል፡፡የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ የቃሉን እውነት በልብህ እንድትሰውር ይረዳሀል፡፡የተግባር ስራው የተማርከውን ሁሉ በሚገባ ተግባራዊ እንድታደርገው ይረዱሀል፡፡

በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ኢየሱስ ለአማኞች ሁሉ የሰጠውን የምስራቹን ወንጌል ለዓለም የማድረስ ተልዕኮ እና እራስን ለዚህ ታላቅ ተልዕኮ ስለማዘጋጀት እንዲሁም እንዴት ኢየሱስን ለሌሎች ማስተማር እንደሚቻል ትማራለህ፡፡

እያንዳንዱን ትምህርት በጸሎት ጀምር፡፡መልሶቹን በራስህ አገላለጽ ጻፋቸው፡፡በተገለጠልህ እውነት በሚገባ ትመላለስ እና ትኖር ዘንድ  እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ፡፡ እግዚአብሔር እሱን በማወቅ ይባርክህ፡፡

ማስታወሻ: አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መደበኛ ትርጉም መጠቀም ለዚህ የስልጠና አነስተኛ መጽሐፍ

የተሻለ ነው፡፡

# ትምህርት 1
# ተልዕኳችን

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ኢየሱስ የሰጠን ተልዕኮ ምንድ ነው? ማቴ 28:19-20

2. ደቀመዝሙር ምንድ ነው? ሐዋ 11:26

3. አንድ ሰው እንዴት ደቀመዝሙር ሊሆን ይችላል? ሮሜ 10:9-10, ሉቃ 14: 26-27,33

4. አንድ ሰው ደቀመዝሙር ከሆነ እንዴት ሊኖር ይገባዋል? ሉቃ 9:23, ሮሜ 12:1-2

5. አንድ ደቀመዝሙር ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠንከር በየዕለቱ ምን ማድረግ አለበት? ሉቃ 4:4, ማቴ 26:41

6. አንድ ደቀመዝሙር ለሰዎች የክርስቶስ ኢየሱስ ምስክር ይሆን ዘንድ እንዴት ሊኖር ይገባዋል? ዮሐ13: 35, ማቴ 5:16

7. ደቀመዛሙርት ኢየሱስን በማወቅ ሲያድጉ ሊያውቁ የሚገባቸው የእድገት ደረጃዎች ምንድ ናቸው የእያንዳንዱ የዕድገት ደረጃ ውጤት ምን ይሆናል? 1 ዮሐ 2:12-14

| ደረጃ | ውጤቶች |
|---|---|
| | |

8. "እግዚአብሔርን በማወቅ ስነናድግ," ከህይወታችን ሊወገዱ የሚገባቸው ተግዳሮቶች ምንድ ናቸው? ኤፌ 4:17-5:17

| ሊወገዱ የሚገባቸው | ሊተኩ የሚገባቸው |
|---|---|
| | |

9. በመንፈሳዊ ህይወታችን ስናድግ እግዚአብሔር ሊሰጠን የሚፈልገው መረዳት ምንድ ነው?
   ፊሊ 2:5-8

10. ደቀመዛሙርት ወደ መንፈሳዊ ብስለት ሲያድጉ ሊማሩ የሚገባቸው ምንድ ነው?
   2 ጢሞ 1:9, ኤፌ 5:17

***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ያለው እና ለኢየሱስ የሚኖር ደቀመዝሙር እንድትሆን መጠራትህን ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,እግዚአብሔር ይህንን እውነት እንዲያበራልህ ጸልይ፡፡

2. አንዱ ከክርስቶስ አገልግሎት ዓላማዎች መሀከል ደቀመዝሙር ማድረግ መሆንን ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,እግዚአብሔር ይህንን እውነት እንዲያበራልህ በመጸለይ መሄድ ጀምር፡፡

3. ደቀመዝሙር መሆን በህይወትህ ብቸኛው እውነተኛ መንፈሳዊ እድገት የምታገኝበት መንገድ እና በህይወትህ የእግዚአብሔርን ዓላማ የምትፈጽምበት መንገድ እንደሆነ ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ እግዚአብሔር ይህንን እውነት እንዲያበራልህ ጸልይ፡፡

4. ደቀመዝሙር መሆን እና ሌሎች "እግዚአብሔርን በማወቅ ያድጉ"; ዘንድ መርዳት፤የጠላት ኃይላትን መምታት እና ክፉውን ማሸነፍን እንደሚያካትት ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,እግዚአብሔር ይህንን ማድረግ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

5. ደቀመዝሙር ነህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,እግዚአብሔር ደቀመዝሙር የመሆን መሻት እንዲሰጥህ ጸልይ፡፡ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ እና ለኢየሱስ መኖርን ጀምር፡፡

**ማስታወሻ:** **ማቴ 28፤18-20** ን በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡

# ትምህርት 2
# ሌሎችን ማስተማር

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. እግዚአብሔር ያድነን እና ለክርስቶስ መኖር እንድንችል የሚጠቀማቸው ሁለት ነገሮች ምንድ ናቸው? ሮሜ 10:17; ዮሐ 16:7-11, 13

2. ሌሎችን ስንረዳ እና የክርስቶስ ምስክር ስንሆን የሚቃወመን ማን ነው? ኤፌ 6:12

3. የሰይጣን ኃይላትን ለማሸነፍ እና ደቀመዛሙርትን ለማፍራት ልንጠቀም የሚገባን ምንድ ነው? 2 ቆሮ 10:4-5, ኤፌ 6:13-18

4. ደቀመዛሙርትን ለማፍራት በቃሉ ምን እንሰራለን፤ስንጠቀምስ ሊኖረን የሚገባ አመለካከት ምንድ ነው? 2 ጢሞ 3:16, 4:2

5. ሰዎች "እግዚአብሔርን በማወቅ ያድጉ"; ዘንድ ለመርዳት እንዴት መጸለይ ይኖርብናል? 1 ጢሞ 2:1-4, ፊሊ 4:6,  ያዕ 5:16

6. የክርስቶስን አስተሳሰብ በአማኞች ውስጥ ለማስረጽ እና የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወታቸው ይፈጽሙ ዘንድ ለማስቻል ምን እንዲያደርጉ እናበረታታቸዋለን? 2 ጴጥ 1:5-11

7. አንድ ደቀመዝሙር በህይወቱ ስለሚያጋጥመው ችግር እና እንዴት መፍታት እንደሚችል የምታስተምረው ምንድ ነው? 1 ጴጥ 1:6-7, ሮሜ 5:3-5

8. ሰዎች "እግዚአብሔርን በማወቅ ስለማደግ"; በሚገባ ከተማሩ ሊያደርጉት የሚችሉት ምንድ ነው? ፊሊ 2:12-13

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. በራስህ አቅምና ችሎታ ከመታመን ይልቅ በመንፈስ ቅዱስ እና በቃሉ ላይ ትደገፋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,አሁን እግዚአብሔር በእሱ ላይ መደገፍ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡
2. ለሌሎች ምስራቹን ወንጌል ስታስተምር የሚቃወህን የዲያቢሎስን ኃይላት ለይተህ ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,አሁን እግዚአብሔር መናፍስትን የመለየት ጸጋ እንዲሰጥህ ጸልይ፡፡
3. የዲያቢሎስን ኃይላት ትመታ ዘንድ ሁሉም መንፈሳዊ የጦር እቃህ በጥንካሬ ተጠብቀዋልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,አሁን እግዚአብሔር በደከምክበት ስፍራ ጥንካሬን እንዲሰጥህ ጸልይ፡፡
4. ሌሎች የዲያቢሎስን ኃይላትን በሚገባ መምታት ይችሉ ዘንድ ደካማ ስፍራቸውን አውቀው እንዲጠነክሩ ትረዳለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር፡፡
5. ሌሎችን ስታገለግል ቃሉን በስርአት እና በአግባቡ ትጠቀማለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር፡፡
6. የዲያቢሎስን ኃይላት ትመታ ዘንድ ከሌሎች ጋር በመሆን በምልጃ እና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ትቀርባለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር፡፡
7. ሰዎች በመንፈሳዊ ህይወታቸው ያድጉ ዘንድ ቃሉን በመጠበቅ እንዲጸኑ ታስተምራለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር፡፡
8. ሰዎች በህይወታቸው አስቸጋሪ ነገሮች ሲያጋጥማቸው የምስጋና ህይወት እንዲኖራቸው ታበረታታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር፡፡
9. ሰዎችን በሚገባ ካስተማርካቸው በኂላ ያለአንተ ድጋፍ መቆም ይችላሉን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ለምን እንደሆነ በማወቅ ለችግሩ መፍትሔ ፈልግ፡፡

**ማስታወሻ**: **ፊሊ 4፤6ን** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡



**ሌሎችን ስለ ኢየሱስ ለማስተማር**
**በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መመላለስ አለብን**

# ትምህርት 3
# የግል ዝግጅት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ሌሎችን ከማስተማራችን በፊት በግላችን ምን ማድረግ አለብን? ማቴ 7:3-5

2. ይህንን ካላደረግን ምን ውጤት ይኖረዋል? 1 ቆሮ 9:27

3. እንደሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሰረት ሌሎችን ለማስተማር ዝግጁ እንሆን ዘንድ ምን ማድረግ አለብን?

ኤፌ 3:4

2 ጢሞ 2:15

መዝ 1

መዝ 119:11

ሮሜ 6:17–18

1ዮሐ 1:1-3

ዕንባቆም 2:2

4. እንደሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሰረት ሌሎችን ለማስተማር እንዴት እንጸልያለን?

ማቴ 26:41

1 ጢሞ 2:1-4

ማቴ 6:9-13

5. እንደሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሰረት መንፈሳዊ የጦር እቃህን እንዴት ትለብሳለህ?

የእውነት ቀበቶ፤ዮሐ 17:17, 2 ዮሐ 4

የጽድቅ ጥሩር፤ ሮሜ 10:9-10; ሉቃ 14:26, 27, 33; 1 ዮሐ 2:29

የሰላሙ ወንጌል መጫሚያ፤ ሮሜ 10:14-15

የእምነት ጋሻ፤ መዝ 33:20-21

የመዳን ራስ ቁር፤ ፊሊ 4:8

የመንፈስ ሰይፍ፤ ዕብ 4:12, 2 ጢሞ 2:15

ጸሎት, የደህንነት ፍላጻ ኤፌ 6:18

6. እንደሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሰረት፤ሌሎችን ስናስተምር ሊኖረን የሚገባ አመለካከት ምንድ ነው? ማር 10:43-45, ዮሐ 13:14-17

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. በህይወትህ የሚያጋጥሙህ ችግሮ ለመፍታት እና ስለ ኢየሱስ ለሌሎች ለማተማር ዝግጁ ነህን? አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,አሁን እግዚአብሔር ማድረግ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

2. ስለ ኢየሱስ ለሌሎች ለማተማር እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት ትዘጋጃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር።
3. የእግዚአብሔር ቃል በሚያዝህ መሰረት የጸሎት ዝርዝር አለህን፤ለራስህ እና ለሌሎች ትጸልያለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር።

4. የእግዚአብሔር ቃል በሚያዝህ መሰረት መንፈሳዊ የጦር እቃህን በአግባቡ ትለብሳለህን? ትጸልያለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር።

5. ሌሎችን ስታስተምር ከመንፈሳዊ የበላይነት ይልቅ ዝቅ ብሎ የሚያገለግል የአገልጋይ አመለካከት አለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,እግዚአብሔር ዛሬ የአገልጋይ ልብ እንዲሰጥህ ጸልይ።

**ማስታወሻ**: **ማር 10፤44ን** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።




ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜያችንን ስናሳልፍ ሌሎችን እናስተምር ዘንድ ያዘጋጀናል።

# ትምህርት 4
# ክትትል

የምታሰላስሉት ማስታወሻ: ርዕሰ ጉዳዩን በማንበብ፤ አሰላስለው (የሚለውን እና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርገው አሰላስል).

**የክትትል ዓላማ**: አዲስ አማኞች ለኢየሱስ ክርስቶስ ይኖሩ ዘንድ በህይወታቸው ከእግዚአብሔር ጋር የጠነከረ ግንኙነት እንዲመሰርቱ ለማስቻል ነው።

**የክትትል ዋና ግብ**: አዲስ አማኞችን ለመትከል:

1. የየዕለት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
2. የየዕለት ጸሎት
3. የውኃ ጥምቀት
4. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ህይወት
5. ከሌሎች አማኞች ጋር የሚኖረን ህብረት
6. ለህይወታቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈለግ

**ከአዲስ አማኝ ጋር በመሆን እነዚህን ደረጃዎች አጥናቸው**:

1. ከአዲስ አማኝ ጋር መጀመሪያ ግንኙነት በመፍጠር ክትትል አድርግ።ግንኙነታችሁን ለማሳደግ እና የእግዚአብሔርን ቃል የምትካፈሉበትን ጊዜ ለመወሰን ጋብዛቸው ወይም ደውልላቸው (የሚቻል ከሆነ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ) ...

2. በመጀመሪያው ግብዣ "**በየዕለት ህይወት እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ**" ከሚለውን አነስተኛ መጽሐፍ ትምህርት 1ን በማካፈል ጀምር።

3. ከሌሎች የክርስቶስ አማኞች ጋር የአንድነት ጊዜን አዘጋጅ ወይም ጋብዛቸው።

4. የሚቻል ከሆነ በሳምንት ሁለት ጊዜ እስኪጠነክሩ ድረስ ተገናኝታችሁ ቃሉን የምትካፈሉበት ጊዜ ይኑራችሁ።

5. በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ እንዲኖራቸው፤የውኃ ጥምቀት እንዲወስዱ፤በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ህይወት እንዲኖሩ እና በህይወታቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈልጉ አበረታታቸው።

6. እራስህን ለማማከር ወይም ሌሎችን በሚያስፈልጋቸው ነገር ለመርዳት ተዘጋጅ።

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

6. በትምህርቱ የተሰጡትን መመሪያዎች በአግባቡ ትጠቀማለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር።

ተግባራዊ ሥራ: የተሰጡትን መመሪያዎች በመጠቀም ሰዎችን ማስተማር ጀምር።

# ትምህርት 5
# በድጋሚ ሊታወሱ የሚገባቸው ነጥቦች

*የምታሰላስሉት ማስታወሻ: ርዕሰ ጉዳዩን በማንበብ፤አሰላስለው (የሚለውን እና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርገው አሰላስል).*

***አላማችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርትን ማፍራት ነው:*** *ማቴ* 28:18-20 *ተልዕኳችን ደቀመዛሙርትን (በየዕለቱ ለኢየሱስ የሚኖሩ) ማፍራት እንደሆነ ይናገራል።ደቀመዛሙርት ለማፍራት መጀመሪያ አንተ ደቀመዝሙር መሆን አለብህ።የእግዚአብሔርን ፍቅር በማስተማር ሌሎችን መርዳት ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሠራውን ስራ እና ሰዎች "እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ" ማስተማርን ያጠቃልላል።*

***አዳዲስ አማኞችን ማስተማር:*** *አዳዲስ የኢየሱስ አማኞችን ስናስተምር የአዲስ ኪዳን ጸሀፍት እንዳስቀመጡት አራት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ማተኮር አለብን፡*

*ሀ. ግላዊ ህይወት*
*ለ. የቤተሰብ ህይወት*
*ሐ. ከሌሎች አማኞች ጋር ያለ ህብረት*
*መ. ለሌሎች ስለ ኢየሱስ መናገር*

*አዳዲስ የኢየሱስ አማኞችን ስናስተምር፤መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ በማስጠናት በህይወታቸው በሚገባ ይተገብሩት ዘንድ መሰረታዊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እናስተምራቸው።*

***ደቀመዝሙር ምንድ ነው:*** *ደቀመዝሙር ሁልጊዜ ለክርስቶስ ይኖር ዘንድ* ***ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ህብረት*** *ያለው ሰው እንደሆነ አስታውሱ።*

***ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ህብረት የሚከተሉትን ያካትታል:***

*ሀ. ቃሉን (የሕይወት እንጀራ)*
1. *ኤፌ* 3:4 *አንብብ*
2. 2 *ጢሞ* 2:15 *አጥና*
3. *መዝ* 1*አሰላስል*
4. *መዝ* 119:11*አስታውስ*
5. *ዕንባቆም* 2:2 *ጻፍ*
6. *ሮሜ* 6:17-18 *ኑር*
7. *ዮሐ* 1:1-3 *አካፍል*

*ለ. ጸሎት*
1. *በግልህ ማቴ* 26:41 *አጥና*
2. 1 *ጢሞ* 2:1*ለሌሎች አካፍል*

***ለኢየሱስ መኖር የሚከተሉትን ያካትታል:***

*ሀ. ከሌሎች የክርስቶስ አማኖች ጋር* ***ህብረት ማድረግ*** *፤ዮሐ* 13:35
*ለ.* ***ለሌሎች*** *ስለ ኢየሱስ መናገር፤ ማቴ*5:16

***ደቀመዝሙር ከሆንን በመንፈሳዊ ህይወታችን እናድጋለን።*** *ሦስቱ የመንፈሳዊ እድገት ደረጃዎች፤*
1 *ዮሐ* 2:12-14:

***ሀ. ልጅ***
***ለ. ጎበዝ***
***ሐ. ሽማግሌ***

***መንፈሳዊ እድገት የሚያካትታቸው:***

*ሀ. የእርኩሳን መናፍስት ኃይላትን መስበር እና ክፉውን ማሸነፍ፤ኤፌ* 4:17-5:16
*ለ. የክርስቶስን አስተሳሰብ ወይም አዕምሮ መትከል* 2 *ጴጥ* 1:5-10
*ሐ. የእግዚአብሔርን ዓላማ ማወቅ እና በህይወታችን መፈጸም፤* 2 *ጢሞ* 1:9 *እና ኤፌ* 5:17

***ደቀመዝሙርነት የሚያካትታቸው*** *ሰዎች በግል ህይወታቸው ውስጥ ያሉትን እርኩሳን መናፍስት ኃይላትን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ባህላዊ አስተሳሰቦችን ይሰብሩ ዘንድ መርዳት፤ሰዎች ስለግል ህይወት፤የቤተሰብ ህይወት፤የቤተክርስቲያን ህይወት፤እንዲሁም በቃል እና በጸሎት አገልግሎት ውስጥ ስላለው የወንጌል ስብከት የተጻፉ መሰረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆችን እንዲማሩ መርዳት፤እና ለወንጌል አገልግሎት ስራ ማሰልጠን ናቸው።*

***የወንጌል አገልግሎት ከኢየሱስ አገልግሎት የቀጠለ ነው፤****የሚከተሉትን ያካትታል:*

***ሀ. ጸሎት***
***ለ. የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ***
***ሐ. ሰዎች በሚያስፈልጋቸው ነገሮች መርዳት***

*እግዚአብሔር ሰዎች ባለባቸው ችግሮች ላይ ድል መስጠት፤በአገልግሎቱ ሊጠቀምባቸው እና ለዘላዓለም ሊባርካቸው ይፈልጋል።*

***ደቀመዝሙር የሚያደርግ ሰው (ቀደምት መንፈሳዊ ወንድም ወይም እህት):*** *በህይወቱ በጸሎት እና በቃሉ የእርኩሳን መናፍስት ኃይላትን መስበር እና ክፉውን ማሸነፍ እና በፍጹም ልቡ በየዕለቱ ለክርስቶስ መኖር የቻለ ሰው ነው።*

***ደቀመዝሙር የማድረግ ተግባራዊ ስራዎች:***

*ሀ. ስለ አዲስ የኢየሱስ ክርስቶስ አማኝ **መረጃ ሰብስብ** (ስም, አድራሻ, ወዘተ.).*
*ለ. **መጽሐፍ ቅዱስ ወይም አዲስ ኪዳን** በመስጠት ስለአጠቃቀሙ አብራራላቸው።*
*ሐ. **በተቻለ መጠን በስልክ ወይም በደብዳቤ በግል አግኛቸው** (በ24 ጊዜ ውስጥ ቢሆን የተሻለ ነው).*
*መ. በግል ህይወት "እግዚአብሔርን በማወቅ ስለማደግ" ብሎም የቤተሰብ ህይወት፤ከአማኞች ጋር የሚኖረን ህብረት፤እንዲሁም ለሌሎች ስለ ኢየሱስ መናገር የመሳሰሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመሪያዎችን በሚገባ አጥናቸው።*

***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** *በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።*

1. *ደቀመዝሙር ነህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ለመሆን ወስን።*

2. *ሌሎችን ታስተምር ዘንድ በሚገባ ተምረህ በክርስቶስ አድገሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር።*
3. *ሌሎችን ስለ እግዚአብሔር ለማስተማር በዚህ ትምህርት ውስጥ የተሰጡትን መመሪያዎች በመጠቀም በተቻለህ መጠን ተግባራዊ ለማድረግ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ዛሬ ጀምር።*

*ተግባራዊ ስራ: የተሰጡትን መመሪያዎች በመጠቀም ሌሎችን ስለ እግዚአብሔር ማስተማር ጀምር።*

God has a wonderful purpose for your life. We want to help you find and fulfill that purpose. If you would like further training, prayer, or information on how you can work with others to share Jesus where you live; please contact us.

WRITE TO:

BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. BOX 633
Grapevine, TX 76099
U.S.A.

Phone (228) 255-9251

by Email
Send your request to basic@basicministries.com
Or
Visit our web site www.basicministries.com

IF YOU WERE BLESSED BY THIS STUDY SHARE A COPY WITH SOMEONE.
ADDITIONAL COPIES CAN BE DOWNLOADED FROM OUR WEB PAGE www.basicministries.com.

COPIES ARE AVAILABLE IN OTHER LANGUAGES.
CONTACT US FOR MORE INFORMATION.

WOULD YOU LIKE TO KNOW HOW TO MAKE THE WORLD A BETTER PLACE?

WOULD YOU LIKE TO KNOW THE LAST GREAT COMMAND
GOD GAVE MANKIND, AND HOW TO FULFILL IT?

WOULD YOU LIKE TO HELP OTHERS OVERCOME THEIR PROBLEMS?

WOULD YOU LIKE TO KNOW HOW TO HELP OTHERS
LIVE A CONSISTENT VICTORIOUS LIFE?

WOULD YOU LIKE TO SHARE WITH A FRIEND OR LOVED
ONE ABOUT HOW TO "GROW TO KNOW GOD?"

!!THEN THIS BOOK IS FOR YOU!!

Compiled by Henry Pulsifer

This is one of a series of booklets designed to help you live a successful, victorious, life. Henry has experienced the victory that comes from living for Jesus for over 40 years; including God's healing from Cancer as he walked with the cross. Since his healing he has traveled the world sharing Jesus and helping others learn how to find victory and success by living for Jesus, and fulfilling God's purpose for their life.

Out of this experience he has compiled several foundational learning guides which enable people to *grow to know God*, and understand and live the basic Bible principles for success and victory in life. This particular learning guide is designed to show you how you can *grow to know God* by helping others find success and victory in their personal life, as a follower of Jesus. It can also be used to help you teach others, and is appropriate for individuals or groups.

COPYRIGHT 1990 ALL RIGHTS RESERVED
No part of this study may be reproduced without permission from the publisher.
Except,portions may be reproduced if distributed free of charge.
Proper credit should be given for the source of the material.

PUBLISHED BY:

Brothers & Sisters in Christ

BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. Box 633
Grapevine, TX76099
USA

Phone (228) 255-9251
Email basic@basicministries.com
web page www.basicministries.com